# የገንዘብ ሚኒስቴር

# በማሽቃገሪያ ዋጋ የሚደረግን ግብይት ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 981/2016

የገንዘብ ሚኒስቴር
ጥር 2016 ዓ.ም

**መመሪያ ቁጥር 981/2016**

# በማሽጋገሪያ ዋጋ የሚደረግን ግብይት ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ

በገበያ ዋጋ መርህ ባልተደረገ ግብይት ተሳታፊ በሆኑ ተዋዋዮች መካከል የተደረገው ማንኛውም ግብይት በትክክለኛ የገበያ ዋጋ የሚታየውን ገቢ፤ ጥቅም፤ ተቀናሽ፤ ኪሳራ ወይም ማካካሻ ተከትሎ እንዲወሰን ለማድረግ የሚደረገው ማንኛውም ክፍፍል ወይም ድልድል የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት እንደሚከናወን በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ የተደነገገ በመሆኑ፤

ዓለም አቀፍ መልካም ተሞክሮዎችን በተለይም ደግሞ የዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ትብብር ድርጅት የማሽጋገሪያ ዋጋ መመሪያዎችን መሠረት ያደረገና የገበያ ዋጋ መርህን ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል፣ ሁሉን አቀፍ የሆነ በማሽጋገሪያ ዋጋ የሚደረግ ግብይትን ለመቆጣጠር የሚያስችል አሠራር መዘርጋት በማስፈለጉ፣

በፌዴራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 79 (2) እና (4) ለገንዘብ ሚኒስትሩ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “በማሽጋገሪያ ዋጋ የሚደረግ ግብይትን ለመቆጣጠር የወጣ መመሪያ ቁጥር 981/2016” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር የሚከተሉት ቃላትና ሐረጎች ከዚህ በታች የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል።

1/ “የሚነጻጸሩ ግብይቶች” ማለት በዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 መሠረት ሊነጻጸሩ የሚችሉ ግብይቶች ናቸው።

2/ “ቁጥጥር የተደረገበት ግብይት” ማለት ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የሚደረግ ማንኛውም ግብይት ነው።

3. “የሀገር ውስጥ ግብይት” ማለት በግብር ከፋዮች መካከል በአገር ውስጥ የሚደረግ ማናቸውም ግብይት ነው፡፡

4/ “የተግባር ትንተና” ማለት ጥቅም ላይ የዋለውን ንብረት እና ሊደርስ የሚችለውን አደጋ ከግምት ውስጥ በማስገባት በእያንዳንዱ ሰው ከተከናወነው ግብይት ጋር በተያያዘ በተከናወኑ ተግባራት ላይ የሚደረግ ትንተና ነው፡፡

5/ “አዋጅ” ማለት የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ነው፡፡

6/ “ዓለም አቀፍ ግብይት” ማለት በግብር ከፋይና ነዋሪነቱ በኢትዮጵያ ባልሆነ ሰው መካከል የሚደረግ ግብይት ነው፡፡

7/ “ነዋሪ ያልሆነ” ማለት በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ነው፡፡

8/ “ሰው” ማለት በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 2(26) ሥር የተሰጠዉን ትርጉም ይኖረዋል፡፡

9/ “ግንኙነት ያላቸው ሰዎች” የሚለው ሃረግ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 4 የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

10/ “ነዋሪ” ማለት በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 5 ሥር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

11/ “የታክስ ባለስልጣን” ማለት የፌዴራል ወይም የክልል የታክስ ባለስልጣን ነው፡፡

12/ “ግብር ከፋይ” ማለት በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 2(22) የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

13/ “ሙከራ የተደረገበት ሰው” ማለት ቁጥጥር በተደረገበት ግብይት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ በፋይናንስ ጠቋሚው ላይ መልሶ የመሸጫ ዋጋ፣ የተጨማሪ ወጪ ወይም የግብይት የተጣራ ትርፍ ዘዴን በመጠቀም ሙከራ የተደረገበት ሰው ነው፡፡

14/ “ግብይት” ማለት

ሀ) የዕቃዎች ግዢና ሽያጭ፣

ለ) የካፒታል ዕቃዎችን ጨምሮ ግዙፋዊ ሀልዎት ያላቸውን ዕቃዎች መግዛት፣ መሸጥ፣ ማከራየት ወይም መጠቀም፣

ሐ) ግዙፋዊ ሀልዎት የሌላቸውን ሀብቶች መግዛት፣ መሸጥ፣ ማከራየት ወይም መጠቀም፣

መ) የአገልግሎቶች አቅርቦት፣

ሠ) የፋይናንስ አቅርቦትና ከፋይናንስ ጋር የተያያዙ አገልግሎቶችን መስጠት፣

ረ) የታክስ ከፋዩን ታክስ የሚከፈልበት ገቢ ሊነካ የሚችል እስከሆነ ድረስ የተጻፈ ቢሆንም ባይሆንም ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተከናወነ ሌላ ማናቸውም ግብይት ወይም ተከታታይነት ያለው ግብይት፤ ማናቸውም ውል ወይም የማመቻቸት ተግባር፤

15/ "ቁጥጥር ያልተደረገበት ግብይት" ማለት ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል የሚደረግ ማንኛውም ግብይት ነው፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 79(1) በተመለከተው መሠረት ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል በሚደረግ ማንኛውም ዓለም አቀፍ ግብይት ወይም አመታዊ ገቢያቸው ከ500,000 ብር በላይ በሆኑ ግንኙነት ባላቸው ግብር ከፋዮች መካከል በሚደረግ የሀገር ውስጥ ግብይት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. የገበያ ዋጋ መርህ

1/ ማንኛውም ግብር ከፋይ ግንኙነት ካለው ሰው ጋር ግብይት በሚፈጽምበት ጊዜ ግብር የሚከፈልበት ገቢውን የሚወስነው ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር በተጣጣመ መልኩ መሆን አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የተጣጣመ ነው የሚባለው በዚህ ግብይት ውስጥ ያሉት ሁኔታዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በሚደረጉ ግብይቶች ውስጥ ከሚታዩት ሁኔታዎች ያልተለዩ የሆኑ እንደሆነ ነው፡፡

3/ ቁጥጥር የተደረገባቸው ግብይቶች ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውና ማናቸውም የዋጋ ማስተካከያ መጠን የሚወሰነው በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል፡፡

## 5. ተነፃፃሪነት

1/ አንድ ቁጥጥር ያልተደረገበት ግብይት ቁጥጥር ከተደረገበት ግብይት ጋር የሚነፃፃር ነው የሚባለው፡-

ሀ) አግባብነት ባለው የማሽጋገሪያ ዋጋ መወሰኛ ዘዴ መሠረት የሚመረመረውን የፋይናንስ ጠቋሚ ትርጉም ባለው መልኩ በማይነካ ሁኔታ በሁለቱ ግብይቶች መካከል ልዩነቶች የሌሉ እንደሆነ፣

ለ) ልዩነቶች በሚኖሩበት ጊዜ፣ ልዩነቶቹ በንፅፅሮቹ ላይ የሚያስከትሉትን ውጤት ለማስወገድ የሚያስችል እና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ለማነጻጸር የሚያግዝ ማስተካከያ አግባብነት ባለው ቁጥጥር ባልተደረገበት ግብይት የፋይናንስ ጠቋሚ ላይ የተደረገ ከሆነ ነው፡፡

2/ ግብይቶቹ ለተፈፀሙበት ሁኔታ ኢኮኖሚያዊ አግባብነት እስካላቸው ድረስ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ግብይቶች የሚነጻጸሩ ናቸው ብሎ ለመወሰን የሚከተሉት ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ይገባሉ፡-

ሀ) የንብረቱ ወይም የአገልግሎቱ ባህሪያት፣

ለ) ጥቅም ላይ የዋለውን ንብረት እና የሚጠበቀውን ስጋት ከግምት ውስጥ በማስገባት ግብይቱን አስመልክቶ በእያንዳንዱ ሰው የተከናወነውን ተግባር፣

ሐ) የግብይቶች የውል ቃሎችና የውል ሁኔታዎች፣

መ) ግብይቶቹ የተከናወኑባቸውን የኢኮኖሚና የገበያ ሁኔታዎች፣ እና

ሠ) ግብይቶቹን የፈፀሙት ሰዎች የተከተሏቸውን የንግድ ስልቶች፣

3/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) አፈጻፀም የማነጻጸሪያ ማስተካከያ የሚደረገው የውጤቱን አስተማማኝነት ከፍ ለማድረግ ሆኖ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

ሀ) ማስተካከያው የሚደረግበት ልዩነት መሰረታዊ ሆኖ ሲገኝ፣

ለ) ማስተካከያ የሚደረግበትን መረጃ ጥራት፣

ሐ) የማስተካከያውን ዓላማ፣

መ) ማስተካከያው የሚደረግበትን ዘዴ አስተማማኝነት፡፡

## 6. <u>በማሽጋገሪያ ዋጋ ግብይት ያለመፈፀሙን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ዘዴዎች</u>

1/ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የማሽጋገሪያ ዋጋ ግብይት ያለመኖሩን ለማረጋገጥ የሚከተሉት የተፈቀዱ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

ሀ) **ቁጥጥር ያልተደረገበት ተነጻጻሪ ዋጋ ዘዴ፡-** ይህ ዘዴ ቁጥጥር በተደረገበት ግብይት ውስጥ ለተላለፈ ንብረት ወይም አገልግሎት የተከፈለው ዋጋ ቁጥጥር ባልተደረገበት ግብይት ለተላለፈ ንብረት ወይም አገልግሎት ከተከፈለው ዋጋ ጋር የሚነጻጸርበት ዘዴ ነው፡፡

ለ) **መልሶ የመሸጫ ዋጋ ዘዴ:-** ይህ ዘዴ አንድ ሰው ቁጥጥር በተደረገበት ግብይት የገዛውን ዕቃ መልሶ በመሸጥ ያገኘውን የትርፍ ህዳግ ይህንኑ እቃ ቁጥጥር ባልተደረገበት ግብይት መልሶ ቢሸጥ የሚያገኘውን የትርፍ ህዳግ ለማወቅ በሌሎች ቁጥጥር ባልተደረገባቸው ተነጻጻሪ ግብይቶች ተመሳሳይ ዕቃ ተሸጦ ከሚገኘው የትርፍ ህዳግ ጋር የሚነጻጸርበት ዘዴ ነው።

ሐ) **የተጨማሪ ወጪ ዘዴ፡-** ይህ ዘዴ ቁጥጥር በተደረገበት ግብይት ውስጥ ንብረቶችን ወይም አገልግሎቶችን ለማቅረብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የወጣው ተጨማሪ ወጪ ቁጥጥር ባልተደረገባቸው ግብይቶች ንብረቶችን ወይም አገልግሎቶችን ለማቅረብ ከሚወጣው ተጨማሪ ወጪ ጋር የሚነጻጸርበት ዘዴ ነው፡፡

መ) **የግብይት የተጣራ ትርፍ ዘዴ፡-** በአንድ ግብይት ውስጥ ተሳታፊ የሆነ ሙከራ የተደረገበት ሰው ቁጥጥር በተደረገበት ግብይት ውስጥ ተገቢ በሆነ የገቢ መሰረት (ለምሳሌ ወጪ፣ ሽያጭ፣ ንብረት) ላይ ተመስርቶ የሚያገኘው የተጣራ የትርፍ ህዳግ ፤ቁጥጥር ባልተደረገበት በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ተነጻጻሪ ግብይት ወይም ግብይቶች ውስጥ በተመሳሳይ የገቢ መሰረት ላይ ተመስርቶ ከሚያገኘው የተጣራ ትርፍ ጋር የሚነፃፀርበት ዘዴ ነው።

ሠ) **የግብይት ትርፍን የማከፋፈል ዘዴ፡-** ይህ ዘዴ ቁጥጥር በተደረገበት ግብይት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ሰዎች በጋራ ያገኙት ትርፍ ወይም ያጋጠማቸው ኪሳራ አንድ ግንኙነት የሌለው ሰው ቁጥጥር ባልተደረገባቸው ተነጻጻሪ ግብይቶች በመሳተፍ የሚጠብቀውን ትርፍ ወይም ኪሳራ መሰረት በማድረግ ለእያንዳንዱ ሰው የሚደለደልበት ዘዴ ነው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከሀ-መ የተገለጹትን ዘዴዎች በመጠቀም በአንዱ ወይም በሁለቱም ግንኙነት ባላቸው ሰዎች የተከናወኑ የተወሰኑ ተግባራት የገበያ ዋጋን የተከተሉ መሆናቸውን መወሰን የሚቻል ከሆነ፤ እነዚህ ተግባራት ተለይተው ከታወቁ በኋላ የሚደረስበትን ቀሪ የጋራ ትርፍ ወይም ኪሳራ መሠረት በማድረግ የግብይት ትርፍን የማከፋፈል ዘዴ ተግባራዊ ይደረጋል። በዚህ ንኡስ አንቀጽ መሰረት ትርፍን ወይም ኪሳራን የማከፋፈል ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ የገበያ ዋጋ መርህ መከበሩን ለማረጋገጥ የሚከናወነው የማከፋፈል ተግባር የሚመራበት መስፈርት

የጉዳዩን የተለዩ ባህሪያት መከተል ያለበት ሲሆን፤ መስፈርቱ ግንኙነት ለሌላቸው ሰዎች የተከናወነውን ሽያጭ እና የተደረገውን ወጪ የመሳሰሉ ተጨባጭ መረጃዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያለበት ሲሆን፤ ቁጥጥር ከተደረገበት ግብይት ጋር የተያያዙ መረጃዎችን መጠቀም የለበትም፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ቢኖርም አንድ ታክስ ከፋይ በማሸጋገሪያ ዋጋ ግብይት ያለመፈፀሙን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ከሚውሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተዘረዘሩት ዘዴዎች ውጪ ለመጠቀም የሚችለው ከተዘረዘሩት ዘዴዎች የትኛውም ቁጥጥር በተደረገበት ግብይት ውስጥ ያለውን የገበያ ዋጋ ለመወሰን የማያስችል ሲሆን እና ግብር ከፋዩ የሚጠቀምበት ሌላ ዘዴ የሚያመጣው ውጤት ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የሚጣጣም ሲሆን ነው፡፡

## 7. <u>በማሸጋገሪያ ዋጋ ግብይት ያለመፈፀሙን ለማረጋገጥ የተፈቀዱ ዘዴዎች አጠቃቀም</u>

1/ ቁጥጥር በተደረገበት ግብይት የሚታዩት ሁኔታዎች ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸው የሚወሰነው የጉዳዩን ፍሬነገሮች እና ሁኔታዎች መሰረት በማድረግ የበለጠ ተገቢ የሆነውን ዘዴ ተግባራዊ በማድረግ ነው፡፡

2/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 (1) ሥር ከተመለከቱት ዘዴዎች መካከል የበለጠ ተስማሚ የሆነው ዘዴ የሚመረጠው የሚከተሉትን መስፈርቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት መሆን አለበት፣

ሀ) የእያንዳንዱን የተፈቀደ ዘዴ አንጻራዊ ጠንካራና ደካማ ጎን በማየት፣

ለ) ቁጥጥር ከተደረገበት ግብይት ባህሪይ አንጻር ተቀባይነት ያገኘው ዘዴ አግባብነት ከግምት ውሰጥ የሚገባው የተከናወኑትን ተግባራት፣ ጥቅም ላይ የዋሉትን ንብረቶች እና የተወሰደውን ስጋት መሰረት በማድረግ እያንዳንዱ ሰው ቁጥጥር በተደረገበት ግብይት ውስጥ ምን ተግባር እንዳከናወነ ትንተና በማድረግ ፤

ሐ) የተመረጠውን የማሸጋገሪያ ዘዴ ተግባራዊ ለማድረግ የሚጠቅም አስተማማኝ መረጃ መኖሩን በማረጋገጥ፣

መ) ቁጥጥር በተደረገበትና ቁጥጥር ባልተደረገበት ግብይት መካከል ያለውን ልዩነት ለማስወገድ ጥቅም ላይ የሚውለውን የንጽጽሮሽ ማስተካከያ አስተማማኝነት፤ ካለ፤ ጨምሮ በሁለቱ መካከል ያለውን የተነጻጻሪነት መጠን፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩት መስፈርቶች ግምት ውስጥ ገብተው፣ በአንቀጽ 6(1)(ሀ) እና በአንቀጽ 6(1) ከተራ ፊደል (ለ) እስከ (ሠ) ሥር ከተዘረዘሩት ዘዴዎች አንዱ በእኩል አስተማማኝነት ደረጃ ተግባራዊ የሚሆን ከሆነ በአንቀጽ

6(1(ሀ) የተመለከተው ዘዴ ተግባራዊ ይደረጋል። በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከቱት መስፈርቶች ግምት ውስጥ ገብተው በአንቀጽ 6(1) ከ(ለ-ሐ) ከተመለከቱት ዘዴዎች አንዱ እና በአንቀጽ 6(1) ከ(መ-ሠ) ከተመለከቱት ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ከሌላው ጋር በእኩል ደረጃ አስተማማኝ ከሆኑ በአንቀጽ 6(1)(ለ) እና (ሐ) የተመለከተው ዘዴ ተግባራዊ ይሆናል።

4/ የአንድ ቁጥጥር የተደረገበት ግብይት ሁኔታዎች ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ለመወሰን ከአንድ በላይ የማነፃፀሪያ ዋጋ ዘዴ መጠቀም አይቻልም።

5/ ማንኛውም ግብር ከፋይ ከተፈቀዱ ዘዴዎች አንዱን ተጠቅሞ የተገኘ እና የዘዴው አመራራጥ ከዚህ አንቀጽ ጋር የተጣጣመ ሆኖ ከተገኘ የታክስ ባለስልጣን ቁጥጥር በተደረገበት የግብር ከፋዩ ግብይት ውስጥ ያሉት ሁኔታዎች ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ምርመራ በሚያደርግበት ጊዜ በግብር ከፋዩ የተመረጠው ዘዴ የበለጠ አግባብነት የሌለው መሆኑ ካላረጋገጠ በስተቀር በግብር ከፋዩ የተመረጠው ዘዴ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

## 8. <u>ሙከራ የሚደረግበትን ሰው ስለመምረጥ</u>

የተጨማሪ ወጪ፣ መልሶ የመሸጫ ዋጋ ወይም በአንቀጽ 6 የተመለከተው የግብይት የተጣራ ትርፍ ዘዴ ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ ሙከራ የሚደረግበትን ሰው የመምረጡ ሂደት ከግብይቱ የተግባር ትንተና ጋር የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል።

## 9. <u>ቁጥጥር የተደረገባቸውን ጥምር ግብይቶች ስለመገምገም</u>

አንድ ግብር ከፋይ በተመሳሳይ ሁኔታዎች ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ቁጥጥር የተደረገባቸው፣ ኢኮኖሚያዊ ትስስር ያላቸው እና ለየብቻቸው በአስተማማኝ ሁኔታ ሊተነተኑ የማይችሉ ግብይቶች ያደረገ እንደሆነ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 የተመለከተውን የማነጻጸር ተግባር ለማከናወንና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን የማሸጋገሪያ ዋጋ ስሌት ዘዴዎች ተግባራዊ ለማድረግ እነዚህ ግብይቶች ሊጣመሩ ይችላሉ።

## 10. <u>የገበያ ዋጋ መነሻ እና መድረሻ</u>

1/ የገበያ ዋጋ መነሻ እና መድረሻ የሚባለው እንደ ዋጋ፣ የትርፍ ህዳግ ወይም የትርፍ ድርሻ ያሉ አግባብነት ያላቸውን የፋይናንስ ጠቋሚ ቁጥሮች መሠረት በማድረግ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 ከተዘረዘሩት በጣም የተሻለውን የማሸጋገሪያ ዋጋ ስሌት ዘዴ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 በተመለከተው የማነጻጸሪያ ትንተና መሰረት እያንዳንዳቸው አስተማማኝነት እና ቁጥጥር ከተደረገበት ግብይት ጋር በእኩል ተነጻጻሪነት ባላቸው በተመረጡ ቁጥጥር ባልተደረገባቸው ግብይቶች ላይ ተግባራዊ በማድረግ የሚገኘው ውጤት ነው።

2/ ቁጥጥር የተደረገበት ግብይት ወይም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 መሠረት የተጣመሩ ግብይቶች አግባብነት ባለው የማሸጋገሪያ ዋጋ ዘዴ ሙከራ ከተደረገበት እና በገበያ ዋጋ መነሻ እና መድረሻ ውስጥ መሆኑ ከተረጋገጠ ቁጥጥር ከተደረገበት ግብይት ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ግብይቶች የፋይናንስ ጠቋሚ ውስጥ መሆናቸው እስከተረጋገጠ ድረስ በአዋጁ አንቀጽ 79 መሰረት ማስተካከያ አይደረግባቸውም።

3/ አግባብነት ያለው ቁጥጥር የተደረገበት ግብይት ወይም በአንቀጽ 9 መሠረት የተጣመሩ ግብይቶች የፋይናንስ ጠቋሚ ከገበያ ዋጋ መነሻ እና መድረሻ ውጭ የሆነ እንደሆነ የታክስ ባለሥልጣኑ በአዋጁ አንቀጽ 79(1) መሠረት በግብር ከፋዩ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ላይ ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል። ግብር ከፋዩ ወይም የታክስ ባለሥልጣኑ በመነሻ እና መድረሻው ውስጥ ሌላ ነጥብ የበለጠ ተስማሚ መሆኑን ማሳየት ካልቻሉ በስተቀር የዋጋ ማስተካከያው መሰረት የሚሆነው የህዳጉ አጋማሽ ቁጥር ነው።

4/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 አፈጻፀም ሲባል የገበያ ዋጋ መነሻ እና መድረሻ አጋማሽ ቁጥር ተደርጎ የሚወሰደው የገበያ ዋጋ መነሻ እና መድረሻውን ካስከተሉት ቁጥጥር ካልተደረገባቸው ተነጻጻሪ ግብይቶች የሚመነጨው የፋይናንስ ጠቋሚ ቁጥር 50ኛው ፐርሰንታይል ነው። ለዚህም አፈጻጸም ሃምሳኛው ፐርሰንታይል (50%) የሚባለው ከፋይናንስ ጠቋሚው ቁጥሮች ቢያንስ ሃምሳ (50) በመቶው ከዚህ ቁጥር እኩል ወይም የሚያንሱ የሆነ እንደሆነ ነው ። ሆኖም ግን ከውጤቶቹ ሃምሳ (50) በመቶው ከፋይናንስ ጠቋሚው ቁጥር ጋር እኩል ወይም ከዚያ በታች ከሆኑ ሃምሳ (50) በመቶው ከአማካይ ውጤቱ እና ከዚያ ከሚቀጥለው ከፍተኛ ቁጥር ጋር እኩል መሆን አለበት።

5/ የዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 እና 16 እንደተጠበቁ ሆነው፣ በገቢ ግብር አዋጁ አንቀጽ 79(1) መሠረት የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት በማድረግ የዋጋ ማስተካከያ የሚደረገው ማስተካከያው የግብር ከፋዩ ግብር የሚከፈልበት ገቢ እንዲጨምር የሚያደርግ ከሆነ ነው።

## 11. <u>ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ተነጻጻሪ ግብይቶችን የሚመለከቱ የመረጃ ምንጮች</u>

1/ ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ተነፃፃሪ ግብይቶችን አስመልክቶ የሚከተሉት የመረጃ ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉ፡-

ሀ) ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ግብይቶች ሆነው ቁጥጥር በተደረገባቸው ግብይቶች ተዋዋይ ወገኖች ከሆነት ውስጥ አንዱ ቁጥጥር ባልተደረገባቸው ግብይቶችም ተዋዋይ ወገን የሆነበት ቁጥጥር ያልተደረገበት ውስጣዊ ግብይት፤

ለ) ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ግብይቶች ሆነው ቁጥጥር በተደረገባቸው ግብይቶች ተዋዋይ ወገኖች ከሆኑት ውስጥ የትኛውም ወገን ተዋዋይ ያልሆነባቸው ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ውጫዊ ግብይቶች፤

2/ ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ውጫዊ ተነጻጻሪ ግብይቶችን የሚመለከት መረጃ ለግብር ከፋዩ ያልደረሰው ከሆነ በአዋጁ አንቀጽ 79(1) መሠረት የዋጋ ማስተካከያ ለማድረግ ለታክስ ባለሥልጣኑ እንደመነሻ ሆኖ ሊያገለግል አይችልም።

3/ ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ተነጻጻሪ ግብይቶችን የሚመለከት መረጃ በግብር ከፋዩ አማካይነት ለታክስ ባለሥልጣኑ እንዲደርሰው ያልተደረገ እንደሆነ ግብር ከፋዩ አንድ ግብይት ከአዋጁ አንቀጽ 79 ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለማስረዳት ይህንን መረጃ ሊጠቀምበት አይችልም።

4/ ከአንድ አገር ወይም ክልል አካባቢያዊ ገበያ ቁጥጥር ያልተደረገባቸውን ግብይቶች ቁጥጥር ከተደረገባቸው ግብይቶች ጋር ለማነጻጸር የሚረዳ መረጃ ያልተገኘ እንደሆነ በሌላ አካባቢያዊ ገበያ የተደረጉ ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ተነጻጻሪ ግብይቶች በታክሱ ባለሥልጣን ተቀባይነት ሊያገኙ ይችላሉ። ከሌሎች አካባቢ ገበያዎች የተገኙ ተነጻጻሪዎች አስተማማኝነት ከእያንዳንዱ ጉዳይ አንጻር እና እነዚህ ተነጻጻሪዎች በአንቀጽ 5 የተመለከቱትን መስፈርቶችን በሚያሟሉት ልክ እንዲሁም ለንጽጽሩ የሚረዱ አማራጭ የመረጃ ምንጮች ሊኖሩ ያለመቻላቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚወሰን ነው። እነዚህን ተነጻጻሪዎች የሚጠቀሙ ግብር ከፋዮች በተቻለ መጠን በዋጋና በትርፍ ላይ የሚጠበቀውን አካባቢያዊ ተፅዕኖ በሚገባ መገምገም ይኖርባቸዋል።

## 12. <u>የግብይት ዋጋ የመወሰኛ ዘዴን አስቀድሞ መስማማት</u>

1/ የፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 79(2) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አንድ ግብር ከፋይ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሚከናወን ቁጥጥር የሚደረግበት የተወሰነ ግብይት በገበያ ዋጋ መርህ እንዲመራ ማድረግ የሚያስችሉ መስፈርቶችን ለመወሰን ከታክሱ ባለሥልጣን ጋር በግብይት ዋጋ መወሰኛ ዘዴ ላይ አስቀድሞ ስምምነት እንዲደረግ ሊጠይቅ ይችላል። ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ በገንዘብ ሚኒስትሩ በሚተላለፍ ሠርኩለር ይወሰናል።

2/ የግብይት ዋጋ የመወሰኛ ዘዴን አስቀድሞ በሚደረግ ስምምነት ለመወሰን የሚቀርብ ጥያቄ ከሚከተሉት ጋር አብሮ ሊቀርብ ይገባል፤

ሀ) የግብር ከፋዩን የሥራ ዓይነት፣ ቁጥጥር የሚደረግበትን ግብይት ዓይነት እና የቀረበውን ሃሳብ የተፈፃሚነት ወሰን እና የሚቆይበትን ጊዜ፣

ለ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 የተመለከተውን የገበያ ዋጋ መርህ ተከትሎ በግብር ከፋዩ የሚቀርብ ሃሳብ በአንቀጽ 5 መሠረት ለጉዳዩ ወሳኝ ናቸው የሚባሉትን የማነፃፀሪያ መስፈርቶች፣ በአንቀጽ 6 ከተመለከቱት መካከል ለጉዳዩ የበለጠ አግባብነት ያለውን የማስተላለፊያ ዋጋ ዘዴን እና ለወደፊት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሃሳቡን ለማቅረብ ከግምት ውስጥ የገቡ ሁኔታዎችን፣

ሐ) ግብር ከፋዩ በዚህ ስምምነት አፈጻጸም ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆን የሚፈልገውን አገር ወይም አገሮች፤ እና

መ) በታክሱ ባለሥልጣን እንዲቀርቡ የሚጠየቁ ሌሎች ማናቸውንም መረጃዎች

3/ የታክሱ ባለሥልጣን ግብር ከፋዩ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን ቅድመ ሁኔታዎች ሊያሟላ የሚችል መሆኑን እና ከጉዳዩ አንጻር የግብይት ዋጋ የመወሰኛ ዘዴን አስቀድሞ መስማማት የሚያስገኘውን ጥቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት ግብር ከፋዩ ያቀረበውን ጥያቄ በመመርመር ስምምነት ለመፈረም በቀረበው ጥያቄ ላይ ውሳኔ ይሰጣል። የታክሱ ባለስልጣን በቂ ምክንያት ካገኘ ግብር ከፋዩ የግብይት ዋጋን አስቀድሞ የመወሰኛ ስምምነት ለመፈራረም ያቀረበውን ጥያቄውን ላይቀበለው ይችላል።

4/ የታክሱ ባለሥልጣን የቀረበውን ሀሳብ በተናጠል ወይም ግንኙነት ያለው ሰው ከጠቀሰው አገር ወይም አገሮች ጋር በመመካከር ሊቀበለው ይችላል።

5/ የታክሱ ባለሥልጣን በግብር ከፋዩ የቀረበውን ሀሳብ ከተቀበለ ወይም ከግብር ከፋዩ ጋር በሚደረግ ስምምነት መሠረት ማስተካከያ ካደረገበት በኋላ ግብር ከፋዩ ስምምነቱን በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ እስካዋለ ድረስ በስምምነቱ ውስጥ በሚካተቱ ቁጥጥር በተደረገባቸው ግብይቶች ላይ የገበያ ዋጋ የሚወሰነው አስቀድሞ በተደረሰው ስምምነት በተመለከቱ ዘዴዎች እንደሚሆን እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4(2) በተመለከተው መሰረት የማሸጋገሪያ ዋጋ ማስተካከያ እንደማይደረግ ለግብር ከፋዩ ማረጋገጫ ይሰጣል።

6) የግብይት ዋጋ የመወሰኛ ዘዴን አስቀድሞ ለመወሰን የሚደረገው ስምምነት፤ ስምምነቱ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ በሚደረግ በስምምነቱ በተመለከተው ቁጥጥር የሚደረግበት ግብይት ላይ ተፈፃሚነት የሚኖረው ሲሆን፤ በስምምነቱ ለተመለከቱት የግብር አመታት ጸንቶ ይቆያል፤ ሆኖም በማናቸውም ሁኔታ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ከሚቆጠሩ አምስት የግብር ዓመታት በላይ ሊቆይ አይችልም።

7/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 6 የተጠቀሰው ቢኖርም የታክሱ ባለሥልጣን፡-

ሀ) ግብር ከፋዩ በቸልተኝነት ወይም ሆን ብሎ ትክክለኛ ያልሆነ፤ የተሳሳተ መረጃ የሰጠ ወይም ማድረግ የሚገባውን ያላደረገ መሆኑን የተረዳ ወይም ግብር ከፋዩ በስምምነቱ ከተካተቱት ውስጥ መሰረታዊ የሆኑትን ቃሎች እና ሁኔታዎች ያላሟላ መሆኑን ካረጋገጠ ወደኋላ ተፈፃሚነት በሚኖረው አኳኋን ስምምነቱን ሊሰርዘው ይችላል፡፡

ለ) ትክክለኛ ያልሆነ ወይም የተሳሳተ መረጃ የሰጠው ወይም ማድረግ የሚገባውን ያላደረገው ግብር ከፋዩ ያልሆነ እንደሆነ ወይም ግብር ከፋዩ ወሳኝ የሆኑ የስምምነቱን ቃሎችና ሁኔታዎች በበቂ ሁኔታ ያላሟላ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ወይም ለስምምነቱ ወሳኝ የሆኑት አንድ ወይም ከአንድ በላይ ግምቶች ተጥሰው የተገኙ እንደሆነ ወይም ስምምነቱ ተፈፃሚ እንዳይሆን የሚያደርግ የሕግ ለውጥ የተደረገ እንደሆነ ስምምነቱ ለወደፊት ተፈፃሚ እንዳይሆን ሊሠርዝ ይችላል፡፡

8/ የታክሱ ባለሥልጣን የግብይት ዋጋ የመወሰኛ ዘዴን አስቀድሞ ለመወሰን ለሚደረግ ስምምነት አጋዥ እንዲሆኑ በግብር ከፋዩ የሚቀርቡ የንግድ ሚስጥሮችን እና ተጋላጭ የሆኑ ሌሎች መረጃዎችን እና ሰነዶችን ሚስጥራዊነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

# ክፍል ሁለት

## <u>በተለዩ ግብይቶች ላይ ስለሚኖረው ተፈፃሚነት</u>

### 13. <u>የአገልግሎት ግብይቶች</u>

1/ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም “አገልግሎት” ማለት፤ በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን፣ ከአንድ ውል ጋር በተያያዘ የሚሰጥን የፋይናንስ ድጋፍ ጨምሮ ከአንድ ሥራ እና ድጋፍ ጋር ተያይዞ የሚሰጡ መብቶች፣ ጥቅሞች፤ ልዩ መብቶችና አጋዥ ተግባራት ናቸው፡፡

2/ የዚህ መመሪያ ሌሎች አንቀጾች እንደተጠበቁ ሆነው ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የተፈፀመ የአገልግሎት ክፍያ ከገበያ ዋጋ መርሆዎች ጋር የተጣጣመ ነው የሚባለው፡-

ሀ) በእርግጥ ለተሰጠ አገልግሎት የተከፈለ ሲሆን፣

ለ) አገልግሎቱ በተሰጠበት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ የአገልግሎት ተቀባዩን የንግድ ደረጃ ከፍ ለማድረግ የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ ወይም የንግድ ጥቅም የሚያስገኝ ወይም እንዲያስገኝ የሚጠበቅ ሲሆን፣

ሐ) በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ ግንኙነት የሌለው ሰው ከሌላ ግንኙነት የሌለው ሰው የዚህ አይነቱን አገልግሎት ቢያገኝ ለመክፈል ፈቃደኛ ከሚሆንበት

ዋጋ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ወይም በውስጥ አቅም ለራሱ ሊሰጥ የሚችለው ሲሆን፣

መ) የዋጋው መጠን በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ግንኙነት የሌላቸው ሰዎች ተነጻፃሪ አገልግሎትን በተነጻጻሪ ሁኔታ ውስጥ ለማግኘት ከሚስማሙበት ዋጋ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን ነው፡፡

3/ ለአንድ ሰው የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የተጣጣመ ሊሆን የማይችለው ክፍያውን የፈፀመው ግንኙነት ያለው ሰው ክፍያውን የፈጸመው ተቀባዩቹ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ቡድኖች ውስጥ የአክሲዮን ባለቤትነት ጥቅም ያላቸው በመሆኑ ምክንያት ሲሆን ነው፡፡ የዚህ አይነቱ ክፍያ በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን የሚከተሉትን ወጭዎች ወይም የስራ እንቅስቃሴዎች ይጨምራል፡-

ሀ) ለእናት ኩባንያው ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ስብሰባ፣ የእናት ኩባንያውን አክሲዮኖች ለማውጣት እና የእናት ኩባንያውን ተቆጣጣሪ ቦርድ ወጭ ለመሸፈን የመሳሰሉትን ጨምሮ በመጀመሪያ ለተጠቀሰው ሰው እናት ኩባንያ ህጋዊ መዋቅር ሪፖርት ከማቅረብ ጋር በተያያዘ የሚወጡ ወጪዎች እና የስራ እንቅስቃሴዎች፣

ለ) ሪፖርቶችን ማጠቃለልን ጨምሮ የእናት ኩባንያውን ሪፖርት የማድረግ ግዴታ ለመወጣት የሚወጣ ወጪ ወይም የስራ እንቅስቃሴዎች፣

ሐ) የቡድኑ አባላቱ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ በመጀመሪያ በተጠቀሰው ሰው ባለቤትነት ስር ያሉ ካልሆነ ወይም ባለቤት በመሆን የሚገኘው ወይም ሊገኝ የሚችለው ጥቅም ተጠቃሚ በመጀመሪያ የተጠቀሰው ሰው ካልሆነ በስተቀር በአንድ የንግድ ሥራ ቡድን ውስጥ አባል የሆኑ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች በቡድኑ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለሚከናወኑ ተግባራት የሚወጣ ወጪ ወይም ለዚህ ዓላማ ገንዘብ ለማሰባሰብ የሚወጣ ወጪ፡፡

4/ የዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ድንጋጌዎች እደተጠበቁ ሆነው፣ አንድ ሰው ለሌላ ግንኙነት ላለው ሰው የሰጣቸውን የተለዩ አገልግሎቶች ለይቶ ማወቅ የሚቻል ሲሆን፣ ለአገልግሎቱ የተከፈለው ክፍያ ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የተጣጣመ መሆን አለመሆኑ የሚወሰነው እያንዳንዱን አገልግሎት በተናጠል በመውሰድ ይሆናል፡፡

5/ አንድ ሰው አንድን አገልግሎት ለተለያዩ ግንኙነት ላላቸው ሰዎች በጋራ የሰጠ እንደሆነና ለእያንዳንዱ ሰው የተሰጠውን የተወሰነ አገልግሎት መለየት ካልተቻለ ጠቅላላው የአገልግሎት ክፍያ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የድልድል መነሻ

ምክንያቶችን መሠረት በማድረግ ለእያንዳንዱ ጥቅም ላገኘ ግንኙነት ላለው ሰው ይደለደላል፡፡ ለድልደላው መሠረት የሚሆኑት ቁልፍ ነጥቦችም፡-

ሀ) የአገልግሎቶቹን ባህሪይና የተሰጡበትን ሁኔታ ከግምት ውስጥ ማስገባት፣

ለ) አገልግሎቶቹ ሊሰጣቸው የታሰቡት ወገኖች ያገኙትን ወይም ያገኛሉ ተብሎ የሚጠበቀውን ጥቅም ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ መገመት፣

ሐ) ቁጥጥር ያልተደረገባቸውን ግብይቶች መሰረት በማድረግ ቁጥጥር ከተደረገባቸው ጋር ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ቁጥጥር ካልተደረገባቸው ግብይቶች ጋር ማዛመድ፣

መ) ሚዛናዊና አስተማኝ በሆነ ሁኔታ ሊለኩ የሚችሉ መሆናቸውን ግምት ውስጥ ማስገባት፣ ይሆናሉ።

## 14. <u>ግዙፋዊ ህልዎት የሌላቸውን ንብረቶች የሚመለከቱ ግብይቶች</u>

1/ ለዚህ መመሪያ ዓላማ ሲባል፣ ግዙፋዊ ህልዎት የሌላቸው ንብረቶች ግብይቶች የሚባሉት በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን፣ ፓተንትን፣ ቅጂ መብትን፣ ቀመርን፣ አሰራርን፣ ዲዛይንን፣ ሞዴልን፣ ፕላንን፣ የንግድ ምስጢር፣ የዕውቀት፣ የንግድ ምልክትን እና መሰል ንብረቶችን መጠቀም የሚያስችል ፈቃድ መስጠት፣ መሸጥንና ሌላ ማንኛውንም የማስተላለፍን ተግባር የሚጨምሩ ናቸው።

2/ ግዙፋዊ ህልዎት የሌላቸውን ንብረቶች በተመለከተ የሚደረጉ ቁጥጥር የተደረገባቸው ግብይቶች ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ለመወሰን የሚቻለው ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ለግብይቱ ያላቸውን አመለካከት በተለይም ደግሞ በተመሳሳይ ሁኔታ የሚገኙ ግንኙነት የሌላቸው ሰዎች ሊቀበሉ የሚፈቅዱትን ዋጋ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

3/ የዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ድንጋጌዎች ግዙፋዊ ህልዎት በሌላቸው ንብረቶች ግብይቶች ላይ ተፈጻሚ ሲደረጉ ቁጥጥር የተደረገባቸውን ግብይቶች ቁጥጥር ካልተደረገባቸው ግብይቶች ጋር ለማነጻፀር የሚያስችሉ ልዩ ሁኔታዎች ታሳቢ መደረግ ይኖርባቸዋል። እነዚህም ልዩ ሁኔታዎች በእነዚህ ብቻ ሳይወሰኑ የሚከተሉት ናቸው።

ሀ) ግዙፋዊ ህልዎት ከሌለው ንብረት ይገኛል ተብሎ የሚጠበቀውን ጥቅም፣

ለ) ግዙፋዊ ህልዎት በሌለው ንብረት በመጠቀም መብት ላይ የሚጣልን ማንኛውም ጂኦግራፊያዊ ገደብ፣

ሐ) የሚተላለፈው መብት ብቸኛ መብት መሆን ወይም አለመሆን፣ እና

መ) መብቱ የሚተላለፍለት ሰው አስተላላፊው ግዙፋዊ ህልዎት የሌለውን ሃብት የበለጠ በሚያለማበት ጊዜ የመሳተፍ መብት ያለው መሆን አለመሆኑ፣

# ክፍል ሦስት

## ስለሠነድ አያያዝ

### 15. *የማሽጋገሪያ ዋጋን ለመወሰን የሚያዝ ሠነድ*

1/ ማናቸውም ግብር ከፋይ አግባብ ባለው የታክስ ዘመን የተደረጉ ቁጥጥር የተደረገባቸው ግብይቶች ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ወቅታዊ ሰነድ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ሊያዙ የሚገባ ሰነዶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡-

ሀ) የግብር ከፋዩን ታሪክ፣ የቅርብ አመጣጡን እና ወቅታዊውን የገበያ ሁኔታ የሚያሳይ አጠቃላይ መግለጫ የያዘ የንግድ አሠራር አጠቃላይ ዳሰሳ እና የንግዱን አሃዶችን ወይም መምሪያዎችን እና ድርጅታዊ መዋቅሩን የሚያሳይ የአደረጃጀት መግለጫ፤

ለ) ግብር ከፋዩ አባል የሆነበትን ቡድን አባላት፣ ህጋዊ አቋማቸውን ፣ የአክሲዮን መቶኛ ድርሻቸውን የሚጨምር የኩባንያ ድርጅታዊ መዋቅር መግለጫ እና እያንዳንዱ የቡድኑ አባል ከቡድኑ የስራ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ ቁጥጥር የተደረገበትን ግብይት በሚመለከት የሚያከናውነውን ተግባር የሚያሳይን ማብራሪያ ጨምሮ የቡድኑን የስራ እንቅስቃሴ የሚያሳይ አወቃቀር፤

ሐ) በአንቀጽ 5 የተዘረዘሩትን የማነጻፀሪያ መስፈርቶች ጨምሮ ቁጥጥር የተደረገባቸውን ግብይቶች የሚመለከት ማብራሪያ፣

መ) የበለጠ ተስማሚ የሆነውን የማሽጋገሪያ ዋጋ አመራረጥ የሚያሳይ ማብራሪያ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሙከራ የተደረገበት ሰው እና የፋይናንስ ጠቋሚው እንዴት እደተመረጡ የሚያሳይ ማብራሪያ፣

ሠ) ቁጥጥር ያልተደረገባቸውን ተነጻጻሪ ግብይቶችን ለመለየት የተከናወነውን ሂደት የሚያሳይ ማብራሪያ፣ አግባብነት እስካለው ድረስ፤ ማንኛውም ተነጻጻሪ ሊሆን የሚችል ውስጣዊ ግብይት ጥቅም ላይ ያልዋለበትን ምክንያት የሚያስረዳ ማብራሪያ፣ ተነጻጻሪ የሆኑትን ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ግብይቶች የሚመለከት

ማብራሪያ፣ ቁጥጥር ያልተደረገባቸው ግብይቶች የሚመለከት ማብራሪያ፣ የዚህን መመሪያ አንቀጽ 5 ከግምት ውስጥ በማስገባት ቁጥጥር የተደረገባቸውን

ግብይቶች እና ተነጻጻሪ የሆኑ ቁጥጥር ያልተደረገባቸውን ግብይቶች በሚመለከት የተደረገውን ትንተና እንዲሁም የንጽጽሮሽ ዋጋ ማስተካከያ የተደረገበትን ዝርዝር የሚያሳይ ማብራሪያ፣

ረ) የኢንዱስትሪ እና የኢኮኖሚ ትንተና፤ መሠረት የተደረገውን በጀት እና የወደፊት ግምቶችን ዝርዝር፣

ሰ) ቁጥጥር ለተደረገባቸው ግብይቶች ተፈጻሚነት የሚኖራቸው ከሌሎች ሀገሮች ጋር የተፈጸሙ የግብይት ዋጋን አስቀድሞ መወሰን የሚያስችሉ ስምምነቶች ወይም ተመሳሳይ የአሰራር ስርአቶች ዝርዝር፣

ሸ) የዋጋ ማስተካከያዎችን ጨምሮ ቁጥጥር የተደረገባቸው ግብይቶች ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የተወሰዱ እርምጃዎች ማጠቃለያ፤

ቀ) ግብር ከፋዩ ቁጥጥር የተደረገባቸው ግብይቶች የገበያ ዋጋ መርህን የተከተሉ እንዲሆኑ ለማድረግ የወሰዳቸውን እርምጃዎች የሚያሳይ ጉልህ ተፅዕኖ የሚኖረው ሌላ ማንኛውም መረጃ፣

3/ ሰነዱ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ ቋንቋ ሊቀርብ ይችላል።

4/ በአንድ የግብር ዘመን የቀረበ ሰነድ ወቅታዊ ነው የሚባለው በሕግ በተደነገገው የታክስ ማስታወቂያ ጊዜ ውስጥ የቀረበ እንደሆነ ነው።

5/ ማናቸውም ሰነድ በታክስ ባለሥልጣኑ የጽሑፍ ጥያቄ በቀረበ በ45 ቀናት ውስጥ ለታክሱ ባለሥልጣን መቅረብ ይኖርበታል።

6/ የታክሱ ባለሥልጣን በኦዲት ሥርዓት አሠራሩን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መረጃ የመጠየቅ ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ግብር ከፋዩ በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩ ሰነዶችን የማቅረብ ግዴታው ሁልጊዜም የፀና ነው።

## ክፍል አራት

## <u>አስተዳደራዊ ሥነ-ሥርዓቶች</u>

### 16. <u>ለሀገር ወስጥ ግብይቶች የሚደረጉ ተመሳሳይ የዋጋ ማስተካከያዎች</u>

በአዋጁ አንቀጽ 79(1) መሰረት የታክሱ ባለስልጣን በግብር ከፋዩ ታክስ የሚከፈልበት የአገር ውስጥ ግብይት ላይ ማስተካከያ ሲያደርግ፤ ከዚህ ግብር ከፋይ ጋር ግብይት

በፈጸመው በሌላኛው ወገን ታክስ የሚከፈልበት ገቢም ላይ ተገቢውን ማስተካከያ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 17. ለዓለም አቀፍ ግብይቶች የሚደረጉ ተመሳሳይ የዋጋ ማስተካከያዎች

1/ የታክሱ ባለሥልጣን ግብር ከፋዩ የሚያቀርበውን ጥያቄ መሠረት በማድረግ ማስተካከያው ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለማረጋገጥ ምርመራ ሊያደርግ የሚችለው፡-

ሀ) ቁጥጥር የተደረገበት ግብይት ሁኔታዎች በሌላ ሀገር የታክስ አስተዳደር ማስተካከያ ሲደረግባቸው፣

ለ) በሌላ ሀገር የተደረገው የዋጋ ማስተካከያ፤ ቁጥጥር በተደረገበት ግብይት ተሳታፊ የሆነው በኢትዮጵያ ግብር ከፋይ የሆነው ሰው  በዚያው ሀገር ከግብይቱ ባገኘው ትርፍ መጠን ላይ ግብር እንዲከፍል የማድረግ ውጤት የሚኖረው ሆኖ፣ ይኸው ግብር ከፋይ በኢትዮጵያም ግብር እንዲከፍል የተደረገ ሲሆን፤

ሐ) የዋጋ ማስተካከያው እንዲደረግ ሀሳብ ያቀረበው ሀገር ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት የሚያስችል ስምምነት ከኢትዮጵያ ጋር የተፈራረመ ሲሆን፤ ነው፡፡

በዚህ ምርመራ የታክሱ ባለስልጣን የዋጋ ማስተካከያው በመርህም ሆነ በገንዘብ መጠን ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የተጣጣመ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ከደረሰ በዚህ ትርፍ ላይ ግብር ከፋዩ በከፈለው የግብር መጠን ላይ ተገቢውን ማስተካከያ ያደርጋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርበው የማስተካከያ ጥያቄ የታክሱ ባለሥልጣን በውጭ ሀገር የተደረገው ማስተካከያ ከገበያ ዋጋ መርህ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለመወሰን ከሚያስፈልገው መረጃ ጋር ተያይዞ መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ ይህም መረጃ የሚከተሉትን ይጨምራል፡፡

ሀ) ግንኙነት ያለውን ሰው ስም፣ የተመዘገበ አድራሻ፣ አግባብነት ያለው በሚሆንበት ጊዜ የንግድ ስም (ስሞች);

ለ) ግንኙነት ያለውን ሰው የታክስ ነዋሪነት የሚያሳይ ማስረጃ፣

ሐ) ማስተካከያ የተደረገበት ቁጥጥር የተደረገበት ግብይት የተከናወነበትን ዓመት (ዓመታት)፣

መ) ጥያቄ የቀረበበትን በሌላ ሀገር የታክስ አስተዳደር መ/ቤት የተደረገውን ማስተካከያ እና ማስተካከያ የተደረገበትን የገንዘብ መጠን፣

ሠ) የማነጻጸሪያ ትንተና የተደረገበትን መነሻ እና ተግባራዊ የተደረገውን የማሽጋገሪያ ዋጋ ዘዴ ጨምሮ፤ በሌላው ሀገር የታክስ አስተዳደር የተደረገውን የዋጋ ማስተካከያና ማስተካከያው በምን ላይ ተመስርቶ እንደተደረገ የሚያሳይ ማስረጃ፣

ረ) ግንኙነት ያለው ሰው በሌላው ሀገር ህግ መሰረት በታክስ አስተዳደር መስሪያ ቤቱ የተደረገው የዋጋ ማስተካከያ እንዲቀንስ ወይም እንዲሻር ለማድረግ የሚያስችል አቤቱታ አለማቅረቡን ወይም ሊያቀርብ አለመቻሉን የሚገልጽ ማረጋገጫ፤

ሰ) ማስተካከያው ከገበያ መርህ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለመመርመር የሚያስፈልግ ማናቸውም አግባብነት ያለው ሌላ መረጃ፤

3/ ጥያቄው መቅረብ የሚኖርበት ተፈፃሚነት ባለው የታክስ ስምምነት ውስጥ አንድ ጉዳይ በጋራ ስምምነት ላይ ተመስርቶ እልባት ሊያገኝ ይችል ዘንድ ጥያቄ ሊቀርብ በሚችልበት የጊዜ ገደብ ውስጥ ነው፡፡

## 18. ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ድርጅት (OECD) የማሽጋገሪያ ዋጋ ለመወሰን ያወጣው መመሪያ አግባብነት

የዓለም አቀፉ የኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ድርጅት "የብዙሃን-አገሮች ድርጅቶች እና ታክስ አስተዳደሮችን አስመልክቶ ያወጣው የማሽጋገሪያ ዋጋን ለመወሰን የሚያስችል መመሪያ" ይህንን መመሪያ ለመተርጎም እንደ ዋነኛ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ሆኖም ግን የኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ድርጅት መመሪያ ከፌዴራል የገቢ ግብር አዋጁና ከዚህ መመሪያ ጋር የሚጋጭ ሲሆን የገቢ ግብር አዋጁና ይህ መመሪያ የበላይት ይኖራቸዋል፡፡

## 19. አስተዳደራዊ ቅጣት

ማናቸውም ግብር ከፋይ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 15 የተዘረዘሩ ሰነዶችን ያልያዘ ወይም በታክስ ባለስልጣኑ ሲጠየቅ ያላቀረበ እንደሆነ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2016 አንቀጽ 102 መስረት ይቀጣል፡፡

## 20. የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች

1/ በማስተላለፊያ ዋጋ የሚደረግ ግብይትን ለመከላከል የወጣው መመሪያ ቁጥር 231/2013 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

2/ ማንኛውም መመሪያ ከዚህ መመሪያ ጋር የማይጣጣም ከሆነ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 21. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበበት እና በገንዘብ ሚኒስቴር ድህረ ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

*አዲስ አበባ*
*ጥር 2016 ዓ.ም*

*አህመድ ሺዴ*
*የገንዘብ ሚኒስትር*